# ዳይናሚክ ማይክሮፋይናንስ ተቋም አ.ማ.

## የአክሲዮን ሽያጭ ማስታወቂያ

ዳይናሚክ ማይክሮፋይናንስ ተቋም አክሲዮን ማኀበር በአነስተኛ የፋይናንስ ስራ አዋጅ ቁጥር 626/2009 መሰረት ተቋቁሞ ከኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ የስራ ፈቃድ በማግኘት በመስራት ላይ የሚገኝ የፋይናንስ ተቋም ነው። ተቋሙ በ15 ዓመት የአገልግሎት ቆይታው በየጊዜው ሁሉን አቀፍ እድገት በማስመዝገብ ላይ የሚገኝ ሲሆን፤ የካፒታል አቅሙን ለማጠናከር እንዲረዳው በማቀድ ታህሳስ 6 ቀን 2016 ዓ.ም በተካሄደው 6ኛው አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባዔ ላይ የተሻሻለው የንግድ ሕግ አንቀፅ 442 በሚፈቅደው መሰረት እያንዳንዳቸው አንድ ሺ ብር ዋጋ ያላቸው 380 ሺ አዲስ አክሲዮኖችን በማውጣት የአክሲዮን ማኅበሩ ካፒታል አሁን ካለበት ከ **ብር 120 ሚሊዮን (አንድ መቶ ሀያ ሚሊዮን)** ወደ **ብር 500,000,000.00 (አምስት መቶ ሚሊዮን ብር)** እንዲያድግ ተወስኗል።

በመሆኑም በቀረበው የባለቤትነት ጥሪ እድል መሰረት፤

1. ለሽያጭ የቀረበው አዲስ የአክሲዮን ብዛት እንያንዳዳቸው 1,000 ብር ዋጋ ያላቸው 380,000 አዲስ አክሲዮኖች ናቸዉ።
2. የአንድ አክሲዮን ዋጋ ብር 1,000 (አንድ ሺ ብር) ሲሆን፤ አንድ አዲስ ባለአክሲዮን ሊገዛ የሚችለው ዝቅተኛው የአክሲዮን ብዛት 50 (ሃምሳ) ወይም ብር 50,000 (ሃምሳ ሺ ብር) ዋጋ ያላቸው አክሲዮኖችን ነው።
3. እስከ 6ኛው አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባዔ ድረስ ያሉት ነባር ባለአክሲዮኖች ከፕሪሚየም ክፍያ ነፃ መግዛት የሚችሉ ሲሆን አዲስ ባለአክሲዮኖች ግን በአጠቃላይ በማንኛውም ጊዜ ፈርመው በሚገዙት አክሲዮን ላይ የሚታሰብ 5% (አምስት በመቶ) የፕሪሚየም ክፍያ መክፈል ይጠበቅባቸዋል።
4. የአክሲዮን የክፍያ ሁኔታ፤
   4.1. ማንኛውም ኢትዮጵያዊ የሆነ አክሲዮን ገዢ የአክሲዮንና የፕሪሚያም ክፍያ የሚፈፀመው በኢትዮጵያ ብር ነው።
   4.2. ማንኛውም ትውልደ ኢትዮጵያዊ የሆነ የውጪ አገር ዜጋ የአክሲዮንና የፕሪሚያም ክፍያ የሚፈፀመው የብሔራዊ ባንክ መመሪያ በሚፈቅደው መሰረት በውጪ አገር ገንዘብ ይሆናል።
   4.3. ነባርም ሆኑ አዲስ ባለአክሲዮኖች የፈረሟቸውን አክሲዮኖች: ቢያንስ ግማሹን (50%) ክፍያ የአክሲዮን ግዢ በፈረሙበት ቀን፣ ቀሪ አንድ አራተኛውን (25%) ክፍያ የአክሲዮን ግዢ በተፈረመ በ6 ወር ጊዜ ውስጥ፣ እንዲሁም የመጨረሻውን ቀሪ አንድ አራተኛ (25%) ክፍያ የአክሲዮን ግዢ በተፈረመ በአንድ ዓመት ጊዜ ወይም ከዚያ በፊት ከፍለው ማጠናቀቅ ይኖርባቸዋል።
5. ማንኛውም ሰው ለመጀመሪያ ዙር አክሲዮን ለመግዛት ሲመጣ የሚከተሉትን ሰነዶች ማቅረብ ይጠበቅበታል፡-
   5.1. አክሲዮን የሚገዛው ድርጅት ከሆነ ሕጋዊነቱን የሚያሳይ የንግድ ምዝገባ፣ ለዘመኑ የታደሰ የስራ ፈቃድ፣ የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር፣ የመመስረቻ ጽሑፍ፣ የድርጅቱን ሕጋዊ ተወካይ የሚያሳይ ደብዳቤ፣ የተወካይ የታደሰ መታወቂያ/ፓስፖርት/መንጃ ፈቃድ ማቅረብ አለበት።
   5.2. አክሲዮን የሚገዛው ግለሰብ ከሆነ ማንነቱን የሚያሳይ በወቅቱ የታደሰ መታወቂያ/ፓስፖርት/መንጃ ፈቃድ፣ ተወካይ ከሆነ ደግሞ ከሚመለከተው የመንግስት መ/ቤት የተሰጠ የውክልና ሰነድ ማቅረብ አለበት።
   5.3. አክሲዮን የሚገዛው ትውልደ ኢትዮጵያዊ የውጪ ሀገር ዜጋ ከሆነ ቢያንስ ለ6 ወር የሚያገለግል ፓስፖርትና የትውልደ ኢትዮጵያዊ መታወቂያ ካርድ ማቅረብ ይኖርበታል።
6. የአክሲዮን ሽያጭ ክፍያ የሚፈፀመው ለዚህ ተግባር ብቻ በተቋሙ ስም በተከፈቱ የባንክ ሂሳቦች ሲሆን ወደ ባንክ ገቢ የተደረበትን የባንክ ሰነድ (ስሊፕ) ይዞ የአክሲዮኖች ሽያጭ በሚከናወንባቸው ቦታዎች ድረስ በአካል በመቅረብ ወይንም ሕጋዊ ተወካይ በመላክ መግዛት ይቻላል።

| ተ.ቁ | የባንክ ስም | ሒሳቡ የተከፈተበት ቅርንጫፍ | የሂሳብ ቁጥር |
|---|---|---|---|
| 1 | የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ | ልደታ ማርያም | 1000598380857 |
| 2 | አቢሲኒያ ባንክ | ልደታ | 9999857 |
| 3 | አዋሽ ባንክ | ጨፌ ሙዳ | 13231268072400 |
| 4 | ፀሐይ ባንክ | ልደታ | 1003818612 |
| 5 | ቡና ባንክ | ልደታ | 1469501007192 |
| 6 | አባይ ባንክ | ልደታ | 1141111023549220 |
| 7 | የኦሮሚያ ኅብረት ስራ ባንክ | አባ ነፍሶ | 1011100244662 |
| 8 | አማራ ባንክ | ልደታ | 9900027715455 |

ለተጨማሪ መረጃ **ዳይናሚክ ሕንጻ** (ልደታ፤ ባልቻ ሆስፒታል አካባቢ ፀሐይ ባንክ የሚገኝበት) በሚገኘው ዋና መስሪያ ቤት የአክስዮን አስተዳደር፤ ወይም በስልክ ቁጥር +251115579632 በመደወል አስፈላጊዉን ተጨማሪ ማብራርያ ማግኘት ይቻላል።

***" ይህ ማስታወቂያ እንዲተላለፍ በኢትዮጵያ የካፒታል ገበያ ባለስልጣን ተፈቅዷል"***

## ዳይናሚክ ማይክሮፋይናንስ ተቋም አ.ማ.

## 15 ዓመታትን በስኬት!

info@dynamicmfi.com
www.dynamicmfi.com

(+251) 115 156 817
(+251) 115 579 632
(+251) 115 577 285